ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

ቀን ግንቦት 24 2000 ዓ.ም

---

## የቴዲ አፍሮ እስራት ፖለቲካዊ መሆኑን የእነፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ጉብኝት አረጋገጠው፡፡

በዛሬው እለት እሁድ ግንቦት 24 2008 ዓ.ም በፕሮፌሰር ኤፍሬም የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን ቴዲ አፍሮን እስር ቤት በመሄድ ማነጋገሩን የግንቦት ድምጽ ዘጋቢ አሳውቋል፡፡ በጉብኝቱ ወቅት ሽማግሌዎቹ ከቴዲ አፍሮ ጋር ያደረጉት ወይይት ዝረዝሩ ባይታወቅም፣ ታዋቂውን ገጣሚ፣ ሙዚቃ አቀነባባሪና ድምጻዊ አርቲስት እስር ቤት ድረስ ሄደው ሽማግሌዎቹ ማነጋገራቸው የቴዲ ጉዳይ የወያኔ መንግስት እንደሚለው የተራ ወንጀል ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ጉዳይ እንደሆነ ያረጋግጣል በማለት ብዙዎችን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እያነጋገረ እንደሆነ ዘጋቢያችን አሳውቋል፡፡

በማከታተልም ሽማግሌዎቹ ለቴዲ አፍሮ ከወያኔ ኢህአዴግ ይዘውት የመጡት መልእክት ይኑር አይኑር ባይታወቅም፣ መልእክቱ ወያኔ ከእዚህ በፊት እንደ ለመደው በሽምግልና ስም፣ ያለጥፋታቸው ያሰራቸውን ግለሰቦች፣ ያላጠፉትን አጠፋሁ ብለው ይቅርታ እንዲጠይቁና ወያኔ የሰራውን ወንጀል በተበዳዮቹ ላይ ለጥፎ ፕሮፓጋንዳ ለማካሄጃ ሲጠቀምብት ከኖረው ስለቱ ውጭ ሊሆን አይችልም የሚል ግምት እንዳለ ሪፖርተራችን አብራርቷል፡፡ ወያኔ/ኢህአዴግ ቴዲን አፍኖ የሚያሰቃየው፣ የመለስን ጸረ-ኢትዮጵያ መርሃ ግብር ቴዲ በድምጹ እያሰናከለበት ስላስቸገረው እንደሆነና ቴዲን በማሰቃየትና በሽማግሌዎች ሴራ ጥሎ በመዋረድ፣ ከሚወደው ህዝብ ጋር ለማቆራረጥ ታቅዶ እንደሆነ የሚጠነቁሉ አዋቂዎች እየተበራከቱ መምጣታቸውን የደረሰን ሪፖርቱ ጨምሮ ገልጽዋል፡፡